# በአውሮፓ የኢትዮጵያውያን ስፖርትና ባህል ምክር ቤት
# አላማና ዋና ተልዕኮ፤

በአውሮፓ የኢትዮጵያውያን ስፖርትና ባህል ምክር ቤት የበጎ አድራጎትና አትራፊ ያልሆነ ድርጅት ሲሆን የተመሰረተ ውም እ.አ.አቆጣጠር በ2002 ዓ.ም ነው።

የአመሰራረቱ ዋና ፅንሰ - ሀሳብና አላማ ኢትዮጵያውያን ወገኖችን በስፖርትና በባህል በታቀፈ መልኩ በአንድ ላይ ለማ ሰባሰብ ብሎም በቅንነት አንድ ህዝብ የመሆናችንን ስሜት የምንገልጽበት፣ ኢትዮጵያዊ ቤተሰባዊነትን የምናጎለብትበት ከዛም ባሻገር ያለምንም ተፅዕኖ ማለትም በዘር፣ በሐይማኖት፣ በጎሣ፣ በፆታ ብሎም የፖለቲካ አመለካከታችን ተፅዕ ኖ ሳያሳድርብንና በልዩነት ነገር ግን በአንድነት አብሮ መስራትን መርሆአችን በማድረግ በጋራ ሀገራችንን የምናስጠራብ ትን፣ ታሪካችንንና ድንቅ ባህላችንን የምናስተዋውቅበት መድረክ ለመፍጠር ነው።

በአውሮፓ የኢትዮጵያውያን ባህልና ስፖርት ምክር ቤት መጀመሪያ አመሰራረት ፅንሰ - ሃሣብ የፈለቀው በጥቂት መል ካም አሳቢዎች፣ መልካም ምግባረኞች፣ ስለ ወገናቸው መልካም ራዕይ ባላቸው ኢትዮጵያውያን ስፖርተኞችና የስፖር ት ቤተሰቦች በጀርመን ሀገር በፍራንክፈርት ከተማ እ.አ. አቆጣጠር በ1999
ዓ.ም ነበር። ከዚህም በመነሳት ነበር በአውሮፓ ያሉትን ስፖርተኞችና የስፖርት ቤተሰቦች ለማሰባሰብ የተጀመረው ሙ ከራ ሙሉ ለሙሉ ተቀባይነት ያገኘው።
የመጀመሪያው ታሪካዊ ስብሰባም እ.አ. አቆጣጠር በ2002 ዓ.ም
ተደርጎ አጠቃላይ ጉባ ው የስራ አመራር ኮሚቴ መርጧል። በመቀጠልም በአውሮፓ የስፖርትና ባህል ምክር ቤት የበ ላይ ጠባቂነት በ8 (ስምንት) ቡድኖች መካከል
ኦገስት (ነሐሴ) 2003 ዓ.ም ታላቅ የእግር ካስ ውድድር በጀርመን ሀገር በስቱትጋርት ከተማ ተደረገ።

ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ይህ በአውሮፓ የኢትዮጵያውያን ስፖርትና ባህል ምክር ቤት ውድድሮችን በበላይነት እየመራና በ ስሩ ያቀፋቸው ስፖርተኞች፣ የተሳታፊው ቁጥርና የስፖርት ቤተሰቡ ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣት በአ ውሮፓ ህብረተሰብ ዘንድ ታዋቂነትና ገናናነትን እንዲያተርፍ አስችሎታል።

ምክር ቤቱ ከስፖርት ባሻገር በተጨማሪ፣ ስለ ሀገራችን ታሪክና ታላቅ ባህላችን ለውጭው አለም በተለይም ለአውሮፓ ህብረተሰብ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያስተዋወቀ የመጣና ወደፊትም በተለያዩ ጊዜያትና መድረኮች ኢትዮጵያንና ባህሏን በበ ለጠ ለማስተዋወቅ ቋሚ ተጠሪ ሆኖ ለመገኘት ቃል ይገባል።